מדינת ישראל

משרד הבינוי והשיכון

ማኅበራዊ የመኖሪያ ቤቶች ድርጅት ነዋሪዎች ላይ ወሲባዊ ትንኮሳ እና ትንኮላዎች

የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ነጥቦች

ወሲባዊ ትንኮሳ እና ትንኮላ የሰዎች ሰብአዊ ክብርን፣ ነጻነትን፣ ግላዊ መብቶች ብሎም ፆታዊ እኩልነትን ከመጉዳት ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው እንዚህን በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ዐይነት መንገድ በሕግ የተከለከሉ ሥነ ምግባሮች ናቸው።

ማኅበራዊ መኖሪያ ቤቶች ድርጅት (ከዚህ በታች "ድርጅቱ") የድርጅቱ እሴቶች አኳያ ተገቢ ያልሆነን ሥነ ምግባሮች እና ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ማኅበራዊ የመኖሪያ ቤቶች ሠራተኞች ወይንም አብሮን የሚኖርን ማንኛውንም ሰው (ከዚህ በታች "ደንበኞች")ላይ ማሳየት **<u>ያለ አንዳች መታገስ</u>** እርምጃ እንደምንወስድ ድርጅቱ ያሳውቃል።

የእነዚህ ደንቦች ዓላማ በድርጅቱው እና ደንበኞች መካከል ግልጽ የግንኙነት መስመር መፍጠር እና እያንዳንዱ ደንበኛ ወይም ግለሰብ በአካባቢያቸው በቀላሉ ሊደረስባቸው እና ግልጽ መገናኛዎችን ማቅረብ እና ያለ ምንም ማስታወቅ ቅሬታ ማቅረብ ነው።

ቅሬታ ማስገባት የደንበኞቹን መብቶች በማንኛውም መንገድ እንደማይጎዳ ድርጅቱው ግልፅ ያደርገዋል። ማንኛውም የድርጅቱውን ሠራተኛ ምግባር በሚመለከት በማንኛውም ሁኔታ ጥርጣሬ ካለ እኛን እንዲያነጋግሩ እንጠይቃለን።

ወሲባዊ ትንኮሳ ምንድር ነው?

(ሀ) ወሲባዊ ትንኮሳ በወንድ ወይም በሴት በአንድ ወንድ ወይም በአንዲት ሴት ላይ ሊፈጸም ይችላል።

(ለ) በሕጉ መሠረት ወሲባዊ ትንኮሳ ክልክል ከሆኑት ስድስት ባሕርያት አንዱ ነው። እነርሱም እነሆ፡-

1. ወሲባዊ አዘል ድርጊቶችን እንዲፈጽም በማስፈራራት ማሰገደድ
2. አስነዋሪ ድርጊሮች - ደንበኛዋ ሳትስማማ ያለፈቃዷ ለፈፀሙት ወሲባዊ ስሜትን የማነሣሣት ወይም የማርካት ድርጊቶች
3. ለተናኳሹ እንደማይፈልግ ያሳወቀ ሰው ላይ ወሲባዊ አዘል ባሕርይ ያሉአቸው ጥያቄችን በተደጋጋሚ ማቅረብ
4. በተደጋጋሚ በወሲብ ላይ የሚያተኩር ባሕርይ ማሳየት
5. የግለሰብን ወሲባዊነት ወይም የወሲባዊ ዝንባሌ በተመለከተ አስነዋሪ ወይም አዋራጅ ባሕርይ ማሳየት
6. የአንድን ሰው ወሲባዊነት በተመለከተ ፎቶግራፍ፣ ፊልም ወይም ቅጂ ይፋ ማድረጉ ሰውየውን የሚያዋርደው ወይም የሚያሳፍረው ከሆነና ይፋ ለማውጣት ፈቃድ ሳያገኙ ማድረግ

እዚህ ላይ ግልጽ እንዲሆን የምንፈልገው ነገር ቢኖር በነዋሪዎቹ እና በማኅበራዊ መኖሪያ ቤት ድርጅት ወይም በድርጅቱ ሠራተኛ በሙሉ እና/ ወይም በአገልግሎት አቅራቢ መካከል ጥገኝነት በመኖሩ <u>እና ስለዚህም እንደ መተዳደሪያው ደንብ መሠረት ነዋሪዎ ምግባሩ እንደ ወሲባዊ ትንኮሳ እንዲቆጠር ምግባሩ እንደማይስማማት መናገሩ አስፋላጊ አይደለም።</u>

ትንኮላ ምንድን ነው?

1. ሁሉም ጥቃት ወይም ማንኛውም ዓይነት የጥቃት ሙከራ ምንጩ ከወሲባዊ ትንኮሳ የመነጨ ከሆነ ይልቁንም መብትን መከለከል ወይም ማንኛውም ዐይነት መብትን የመከልከል ዛቻ፣ ደንበኛ ወይም ማንኛውም ወኪል አቤቱታ ካቀረበች ወይም ለክስ የረዳች ወይም ወሲባዊ ትንኮሳን በተመለከተ ምስክርነቷን ከሰጠች

ከተጎዳሽ ቅሬታ ለማቅረብ አታመንቺ! አቤቱታውን በሙሉም ሆነ በከፊል በሚከተሉት አማራጭ መንገዶች መሠረት ማቅረብ ትችላለሽ፡-

(1) በደንበኛ ጸረ-ወሲባዊ ትንኮሳ ሹም ቢሮ አማካሪ ታማር ካትዚር አቤቱታውን ያቅርቡ። 03-6930482

(2) በድርጅቱው ድር ጣቢያው በኩል ማመልከት www.amigour.co.il.

(3) በኮንስትራክሽን እና ቤቶች ሚኒስቴር የጾታዊ ትንኮሳ ጉዳዮች ኮሚሽነር የሆኑትን ሚስ ሐናን ናጃራ መንሱር በኢሜይል፡ Harassment@moch.gov.il ወይም በቀጣዩ የመልእክት መላኪያ አድራሻ ሊያገኟቸው ይችላሉ፡

(4) ለወሲባዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ድጋፍ መስጫ ማዕከል በስልክ ቁጥር፡ 1202 - ለሴቶች፣ 1203 - ለወንዶች በመደወል ማመልከት

(5) ለፖሊስ ማመልከት (የወንጀል ክስ)

(6) ለገንዘብ ካሣ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ

- **በድርጅቱ ደንበኞች ዘንድ (ከዚህ በታች "ሹም") ድርጅቱ እና ጸረ-ወሲባዊ ትንኮሳ ሹም አቤቱታውን ለመከታተል በፍጥነትና ያለ አንዳች ማስተጓጎል ለመተግበር ቃል እንገባለን።**
- **አቤቱታውን በምትከታተልበት ወቅትም ሆነ ከዚያን በኋላ ሹሟ አቤቱታ አቅራቢዋ ሙሉ የሆነ ጥበቃ ማድረግ ይልቁንም ደግሞ በተቻለ መጠን ተንኳሹን (ተካሳሹን) የማራቅ ተግባር ታደርጋለች።**

በድርጅቱ ድረ ገጽ ላይ ሙሉ የሆነውን የመተዳደሪያ ደንብ መመሪያዎችን ማንበብ ይችላሉ www.amigour.co.il

ማንኛውም በሴት የተጠቀሰው ወንዱንም የሚያመለክተው ሲሆን የተገላቢጦሹም እንዲሁ